# ስለንግድ ሥራ ት/ቤት  አጭር መግለጫ

2ኛውና  የረጅም ዓመታት ዳይሬክተር የነበሩት አቶ ሰይፉ ፊለቀ ፣የንግድ ሥራ ትምህርት ምሩቃን ማኅበር 25ኛው  ዓመት የብር ኢዮቤሊዮ  በ1960 ዓ.ም ሲከበር ከጻፉት ማስታወሻ የተወሰደ እና በአቶ ጌታቸው አሸኔ የተቀነባበረ

"በ1935 ዓ.ም አገሪቱ ከኢጣሊያን የወረራ ዘመን ተላቃ ሙሉ ነጻነቷን እንደተጎናጸፈች፣የንግድና የቢሮ ሥራ አስተዳደር ሙያ ያላቸው እጅግ ተፈላጊ ነበሩ። በዚህ አጣዳፊ ሁኔታ ላይ ባለሙያዎችን ለማዘጋጀት ሕንጻ ይሠራ፣መሣሪያዎች ይሟሉ ሳይባል በዳግማዊ ምኒልክ  ት/ቤት ግቢ በደባልነት ለሕጻናት ሕክምና ቤትነት ያገለግል የነበረ አንድ ሰፊ ክፍል ተመርጦ የመጀመሪያዎቹ 30 ተማሪዎች በሁለት ክፍል 15/15 ሆነው ለስልጠና ተመልምለው  ትምህርቱን እንዲጀምሩ ተደረገ። መምህራኑም ሁለት ቋሚና ሁለት የትርፍ ጊዜ (part time) መምህራን ነበሩ።"

እነዚህ የመጀመሪያዎቹ ተማሪዎች ቀደም ሲል በአካዳሚ ትምህርት ሻል ያለ ወይም ጥሩ ውጤት ካላቸው መካከል የተመረጡ በመሆናቸው የንግድ ሥራ ትምህርት ኮርሶችን በአንድ ዓመት ስልጠና እንዲያጠናቅቁ ተደርጎ  በ1936 ዓመቱ መጨረሻ ሊመረቁ በቅተዋል።

አብዛኞቹም ወዲያውኑ በኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ (State Bank of Ethiopia) የተቀሩትም በገንዘብ ሚኒስቴር፣በአገር ግዛት ሚኒስቴር እና በትምህርት ሚኒስቴር እንዲሠሩ ተመደቡ። ለተከታታይ 3 ዓመታት እስከ 1937 ስልጠናው በአንድ ዓመት ብቻ የተወሰነ  (crush course) ሲሆን የተመረቁትም 26 ብቻ ነበሩ።

በ1938 ዓ.ም እና በ1939 ዓ.ም ስልጠናው ወደ ሁለት ዓመት ተሻሽሎ የትምህርቱ ስፋትና ደረጃ ከፍ እንዲል ተደረገ፣ት/ቤቱም የዚያን ጊዜው አ/አ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ሕንፃ ውስጥ እንዲዛወርና ተጨማሪ የትምህርት ዓይነቶችን በማከል የተመራቂዎችም ብቃትና ደረጃ  እንዲሻሻል ተደረገ። ከ1940 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የትምህርት ዘመኑ ወደ ሶስት ዓመት አደገ። ከ1946 ዓ.ም በኋላ ግን መደበኛው የትምህርት  ዘመን አራት ዓመት ሆኖ ዘለቀ።

ከ1941 እስከ 1945 ዓ.ም አጋማሽ  የዛሬው ናዝሬት  ትምህርት ቤት በሚኙበት  ቦታ ቀደም ሲል የብሪትሽ ካውንስል ግቢ ወደ ነበረው  ተዘዋወረ። በዚህም ሁኔታ ለዓመታት  ከአንዱ ስፍራ ወደሌላው ቦታ በመንከራተት ዘልቋል።

ከጅምሩ ከ1935 ዓ.ም አንስቶ ለአስራ አምስት  ዓመታት ለትምህርት ቤቱ  እድገትና ብቃት ከፍ ያለ መስዋዕትነትና ያላሰለሰ  ብርቱ ጥረት ያበረከቱት ዳይሬክተር ዶ/ር ዊሊያም ናጊብ ሻሽድ እንደነበሩ መጠቀስ የሚገባንና ለእኚህ ታላቅ ሰው አክብሮታችንን መግለጹ ተገቢ ይመስለኛል። እኚህ የአካዳሚክ ምሁር፣መምህርና ዳይሬክተር ለተማሪዎቻቸው የነበራቸው ፍቅር እጅግ ጥልቅና ፍፁም አባታዊ እንደበር የቀድሞ ተማሪዎቻቸው በታላቅ አክብሮትና የጋለ ስሜት እስከአሁን የሚገልጹት ሀቅ ነው።

ዶ/ር ዊሊያም ናጊብ በአንድ በአንድ ወቅት ባደረጉት ንግግር የመጀመሪያው የትምህርት ቤት ዓላማ በአገሪቱ ጅምር የእድገት ጉዞ ወቅት እጅግ አንገብጋቢ የሆነውን ብቁ የመንግሥትና የንግድ  ድርጅቶችን የሚመሩ አገር በቀል ባለሙያዎችን ማፍራት እንደነበር አስታውሰው፣በዚህ ረገድ የን.ሥ ት/ቤት ምሩቃን ገና ከጅምሩ እጅግ ተወዳጅና ተፈላጊ በመሆናቸው ፣በውጭ አገር ዜጎች ተይዘው ይመሩ የነበሩ ሥራዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ  ተክተው ኃላፊነታቸውን በብቃትና በልበ ሙሉነት በመወጣታቸው፣በምሩቃኑ ውጤታማነት የላቀ ኩራት እንደሚሰማቸውና ልባቸው እንደሚረካ፣ከዚህም የተነሣ በየዓመቱ የትምህርቱን ጥራትና የተማሪዎችን ብቃት በማሳደግ ረገድ ይበልጥ እንዳበረታታቸው ገልጸው ነበር።

ቀደምት ምሩቃኑም ፈጣን-ተቀባይነት ችሎታቸውን በተመደቡበት መሥሪያ ቤቶች ያስመሰከሩ በመሆናቸው በአርአያነታቸው በእጅጉ የሚኮሩ ነበሩ።

በመቀጠልም የቀድሞ ተማሪዎቻቸው ጥንስስ ስለሆነው የንግድ ሥራ ትምህርት ምሩቃን ማህበር በማውሳት፣እንደ ልጆቻቸው የሚያስቡትና የሚያበረታቱት በመሆኑ በወቅቱ ማህበሩ ለሚያሰራው ሕንጻ ገንዘብ በማዋጣት ከመጀመሪያዎቹ ተሳታፊዎች አንዱ በመሆናቸው እራሳቸውን እንደ ትልቅ ባለ ዕድል (ዕድለኛ) አድርገው እንደሚቆጥሩ አስረድተው ነበር።

ከትምህርት ቤቱ ቀደምት መምህራን አንዱ የነበሩት አለቃ ጽጌ ገብረኪዳን በጻፉት ማስታወሻ፣ስለ ትምህርቱና ት/ቤቱ ሲጠቅሱ፤

"አንደኛ የትምህርቱ ስምና ዓይነት ከዚህ ቀደም ተሰምቶ ባለመታወቁ፣ለምሳሌም (Commerce,Book-keeping, Short-hand, Typing, Business Training) ወዘተ በመሆኑ፣ሁለተኛውም ምክንያት በዘመኑ እንደተጀመሩት ት/ቤቶች የግል ሕንጻ ስላልነበረው ፣ወላጆች የሚመስላቸው አስተማሪዎች ስኳሩን እየመዘኑ፣እጣኑን እየዘገኑ፣ጨርቁን እየመተሩ፣ጨውን እየቆነጠሩ ለተማሪዎቹ የሚያስጠኗቸው ነበር" ብለዋል።

አንዳንዶቹ እንዲያውም "ለመነገድ ደግሞ ምን ትምህርት የስፈልጋል፣አንድ ቀን ግፋ ቢል ሁለት ቀን ዓረብ ቤት ሄዳችሁ ብትመለከቱ አይበቃም! ዓረቦቹስ ቢሆኑ ትምህርት ቤት ገብተው ሳይሆን እንዲሁ አይደል እየነገዱ የሚበለጽጉ" እንደሚባል የነበረውን ትዝታቸውን አካፍለውን ነበር።

ይህን ሁሉ የውጭና የውስጥ ትግሮችን ተቋቁሞ ፣ትምህርት ቤቱ ከዓመት ወደ ዓመት ተፈላጊነቱ እየጨመረ፣ዕድገቱን በውጤት እያስመሰከረ ተጓዘ። በዚህም ጉዞው የመጀመሪያዎቹን 20 (ሃያ) ሴት ተማሪዎችን በመስከረም 1941 ዓ.ም ከእቴጌ መነን ት/ቤት መልምሎ ከወንዶች ጋር አንድ ላይ እንዲማሩ ያደረገ የመጀመሪያው የ2ኛ ደረጃ ተቋም ነበር፣15ቱ በልዩ ልዩ ምክንያት ያላጠናቀቁ ሲሆን አምስቱ የመጀመሪያዎቹ ሴት ተማሪዎች በሰኔ 1944 ዓ.ም ለመመረቅ በቅተዋል። እነዚህም በልዩ ልዩ መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ውስጥ በቢሮ ሥራ ተቀጥረዋል። ከዚያም ወዲህ ቁጥራቸው በርከት ያሉ ልጃገረድ ተማሪዎችን በመቀበል ያሰለጥን የነበረ ተቋም ሆኖ ይገኛል።

እዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው የአማርኛ የጽሕፈት መኪና በሥራ ላይ እንዲውል የመጀመሪያውን ቀዳሚ እርምጃ የወሰደና ከብዙ ሙከራና ማሻሻያዎች በኋላ በትምህርት ቤቱ ሥራ ላይ እንዲውል ያደረገ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት እንደነበር ነው።

ይህም በመሆኑ በመንግሥት መስሪያ ቤቶች እንዲለመድና እንደ ብርቅ ዕቃ እንዲወደድ ት/ቤቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

በ1949 ዓ.ም ት/ቤቱን አሁን ወዳለበት በራስ አበበ አረጋይ መንገድ በተለምዶ ሰንጋ ተራ ተብሎ በሚጠራው ሠፈር የራሱ የሆነው ሕንፃ ውስጥ ተዘዋወረ፣በወቅቱ የሕንጻው ማማርና የተማሪዎቹ ግራጫና ጥቁር ሰማያዊ ዩኒፎርም ልዩ ክብርና ሞገስን ያጎናጸፈው በመሆኑ ተማሪዎቹም ሆነ መምህራኑ ልዩ ኩራት ይሰማቸው ነበር።

ከ1951 ዓ.ም ጀምሮ በዶክተር ዊሊያም ናጊብ ምትክ ዋና ዳይሬክተር /የት/ቤቱ ዲን/ በመሆን የተረከቡት አቶ ሰይፉ ፈለቀ፣የትምህርት ቤቱን መልካም ዝናና ክብር በማስጠበቅ እጅግ የጣሩ ተወዳዳሪ የሌላቸው ታላቅ ሰው ነበሩ። የአቶ ሰይፉ ፈለቀና የኮሜርስ ስም እጅግ የተቆራኘ በመሆኑ ብዙ ወዳጆቻቸው ሰይፉ የኮሜርሱ በሚል ስያሜ ይጠሩዋቸው ነበር። ይህንንም ለእርሳቸው ያላቸውን አድናቆት/ምስክርነት አለቃ ጽጌ ገ/ኪዳን በአንድ ወቅት የሚከተለውን ስንኝ ቋጥረው አቅርበውታል።

"ከትምህርት ቤቶች ፣ይህ የንግድ ሥራ፣
የሚያስመሰግን ነው ደግሞም የሚያኮራ"
የሰው ልጅ ጠላቶች፣ያገር ጉስቁልና፣
ድህነት፣ምቀኝነት፣ደግሞም ድንቁርና፣
ከወጣቶቻችን ፈጽሞ እንዲጠፉ፣
ከናጊብ ተወልዶ አደገ በሰይፉ።

ትምህርት ቤቱ በሞዴልነት የሚገለገልባቸው ልዩ ልዩ ተቋማትን በማደራጀት ለምሳሌ Language & Office training laboratory, Office supplies shop, Students school Bank, Buffet Club, ወዘተ የተባሉትን በከፊል በተማሪዎች የአክሲዮን ድርሻ የተቋቋሙ የገሀዱ ዓለም የንግድ ሥራ ተምሳሌት የነበሩ መለስተኛ ድርጅቶችን አቋቁሞ ነበር። በነዚህም ተቋማት ተማሪዎቹ እያገለገሉ ሥልጠና ይወስዱ ነበር።

የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት በየጊዜው እድገትን እያስመዘገበ አሁን ላለበት ከፍተኛ ደረጃና እውቅና እንዲበቃ ያደረጉት ፣በየዓመቱ ከትምህርት ቤቱ የሚመረቁት ተማሪዎች ውጤታማነት ሲሆን፣በአስተማማኝ መሠረት ላይ ፀንቶ እንዲቆይ ያረጉት ቀደምት መሪዎቹ ዶክተር ዊሊያም ናጊብ እና አቶ ሰይፉ ፈለቀ ነበሩ።

የነዚህ የት/ቤቱ ቀደምት መሪዎች የሥራ ዘመን 41 ዓመታት ያስቆጠረ ነበር። አሁን ት/ቤቱ ከተመሠረተ 67 ዓመት ሆኖታል። በአሁኑ ወቅት ደረጃውን ወደ ድግሪ ከፍ በማድረግ ወደ ስድስት ፋክሊቲዎችን አስፋፍቶ ይገኛል።

በመሆኑም በየዘርፉ የሰለጠኑ የንግድ አስተዳደር ባለሙያዎችን በማፍለቅ ለአገር ኢኮኖሚ ግንባታ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እያደረገ እንዳለ ይታመናል። በቅርቡም የማስተርስ ዲግሪ ፕሮግራም/ድህረ ምረቃ/ ከፍቶ በHuman Resources Management መስክ ለማስተማር ዝግጅት ላይ እንደሚገኝ ተረድተናል።

ከመጀመሪያዎቹ 1936 ዓ.ም ምሩቃን አንስቶ እስከ አሁን ድረስ ከዚህ የትምህርት ተቋም ተመርቀው ስለወጡ ተማሪዎች ባለን መረጃ መሠረት 75,000 የሚጠጉ ሲሆን ምሩቃኑም በልዩ ልዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በከፍተኛ የኃላፊነት ደረጃ እንዲሁም የብዙ ግል ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት መሥራቾችና የቦርድ አባላት በመሆን በአገር ኢኮኖሚ ግንባታ እና በአህጉራዊ የልማት ተቋማት እጅግ የሚያኮሩ አስተዋጽኦ ያበረከቱና በማበርከትም ላይ የሚገኙ ናቸው። በየትኛውም ክፍለ ዓለም እና በየትኛውም ቢሮ የኮሜርስ የቀድሞ ተማሪ የሌለበት ሥፍራ አይገኝም ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ስለዚህም የንግድ ሥራ ት/ቤት/ ኮሌጅ ተማሪዎች በተመረቁበት እጅግ ፈታኝ ስልጠና (Rigorous training) እንደወርቅ ቀልጠው ፣ጠርተውና ተፈትሸው ስለሚወጡ በየተሰማሩበት የሥራ መስክ ብቃታቸውንና ችሎታቸውን በእጅጉ ያስመሰከሩ ናቸው።